## ከፋኩልቲውና ፡ ከሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጆች ፡ ቦርድ ፡ የቀረበ ፡ ዲን ፡ ፖልን ፡ የመሰናበቻ ፡ መልእክት ።

የዚህ ፡ መጽሔት ፡ እትም ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከተከፈተ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ መሙላቱንና ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ቆርቋሪና ፡ ዲን ፡ ጄምስ ፡ ሲ ፡ ኤን ፡ ፖል ፡ ከሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መልቀቃቸውን ፡ ያመለክታል ። የሕግ ፡ መጽሔት ፡ አዘጋጆች ፡ ቦርድና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ ለፈጸሟቸው ፡ ብዙ ፡ ተግባሮች ፡ ዲን ፡ ፖል ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ለማመስገንና ፡ መልካም ፡ ምኞታቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ እድል ፡ አግኝተዋል ።

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ያወቁት ፡ ሰዎች ፡ ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ለመቆርቆር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ጥረት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ለማወቅ ፡ ያስቸግራቸው ፡ ይሆናል ። ዲኑ ፡ መጀመሪያ ፡ እዚህ ፡ ሲመጡ ፡ ማለት ፡ ባ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በበጋው ፡ ባዶ ፡ የነበረው ፡ የተዘጋ ፡ ቤት ፡ አሁን ፡ በጥሩ ፡ አኳኋን ፡ በመካሄድ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ይዟል ። ገና ፡ ሲጀመር ፡ እንደምንም ፡ ተብሎ ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ተማሪዎች ፡ ተመረጡ ፡ የትምህርት ፡ መምሪያ ፡ (ካሪኩለም) ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ለመጻሕፍት ፡ ቤቱ ፡ መጽሐፍ ፡ መሰብሰብ ፡ ተጀመረ ። ዲን ፡ ፖል ፡ በጥቂት ፡ የሥራ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ እየተረዱ ፡ ሲሠሩ ፡ ቆይተው ፡ አሁን ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤትን ፡ ከአፍሪካ ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ አንዱ ፡ እንዲሆን ፡ አድርገውታል ። ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ ተሠሩ ፡ የምንላቸውን ፡ ማለት ፡ የአስተማሪዎችና ፡ የተማሪዎች ፡ መብዛት ፡ የመጻሕፍት ፡ ቤትና ፡ የመጻሕፍት ፡ መታተም ፡ መስፋፋት ፡ እዚህ ፡ እንዘረዝራቸውም ። ትምህርት ፡ ቤቱን ፡ ለሚያውቁት ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ግልጽ ፡ ናቸው ። ለቀሩት ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መጽሔት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የዲኑን ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫዎች ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ። ሁላችንም ፡ አስተማሪዎች ፡ ተማሪዎችና ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ አፍቃሪዎች ፡ በአለፉት ፡ አራት ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ የተደረገው ፡ አስደናቂ ፡ መሻሻል ፡ በዲን ፡ ፖል ፡ አርቆ ፡ አሳቢነትና ፡ ጠንካራ ፡ መሪነት ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲስፋፋ ፡ ባሳዩት ፡ ቆራጥ ፡ መንፈስ ፡ የተነሳ ፡ መሆኑን ፡ እናውቃለን ። ለዚህም ፡ አስፈላጊነቱ ፡ ፍጹም ፡ ለሆነ ፡ ተግባራቸው ፡ ከልብ ፡ እናመሰግናቸዋለን ።

ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡ እንደሚያውቁት ፡ ዲን ፡ ፖል ፡ ሥራቸውን ፡ ሕግን ፡ በማስተማርና ፡ የሕግን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ በመምራት ፡ አልወሰኑትም ። ከመጀመሪያው ፡ አንስቶ ፡ ዩኒቨርሲቲውን ፡ በሚያደርጓቸው ፡ ተግባሮች ፡ ረድተዋል ፤ ብዙ ፡ እቅዶችም ፡ እንዲጀመሩ ፡ በማነሳሳት ፡ የመጀመሪያው ፡ ናቸው ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የእሳቸው ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ ተማሪዎች ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሆኖ ፡ ማገልገል ፡ አስደናቂ ፡ ውጤትን ፡ አሳይቷል ። ስለዚህ ፡ ዲን ፡ ፖል ፡ በጠቅላላው ፡ ጥለውን ፡ መሄዳቸው ፡ ቀርቶ ፡ የዩኒቨርሲቲው ፡ የአካዳሚክ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንትነትን ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡ የሚያኮራን ፡ ነው ። በወደፊት ፡ ሥራቸውም ፡

ላይ ፡ የሚያጋጥሟቸውን ፡ አስቸጋሪ ፡ ጉዳዮች ፡ በሚገባ ፡ ለማከናወን ፡ እንዲችሉ ፡ ከልብ ፡ እንመኝላቸዋለን ።

በተጨማሪም ፡ የዩል ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ከዊንቲን ፡ ጆንስተን ፡ አዲሱ ፡ የሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ዲን ፡ ሆነው ፡ መሾማቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ እንወዳለን ። ዲን ፡ ጆንስተንን ፡ እንኳን ፡ ደህና ፡ መጡ ፡ እያልን ፡ አዲሱ ፡ ሥራቸው ፡ የሚያነቃቃና ፡ ተስማሚ ፡ እንዲሆንላቸው ፡ እንመኝላቸዋለን ። በኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ማሻሻል ፡ ለሆነው ፡ ለጋራ ፡ ዓላማችን ፡ ከእርሳቸው ፡ ጋር ፡ የመሥራት ፡ እድል ፡ የምናገኝበትን ፡ ጊዜ ፡ በመጠባበቅ ፡ ላይ ፡ ነን ።